«ፍኖተ ሕይወት» በአባ ማትያስ ሊቀ ጳጳስ ዘሀገረ ካናዳ

□□□

ተረክቦ እግዚአብሔርም ማለት መለኮት ከማለት ጋር አንድ ሲሆን ልዩነት እንዳለው ይናገራል:: እንዲሁም የሥላሴ መንግሥት በአካል ከሦስት የማይከፈል አንድ መሆኑን ይናገራል:: «አብ» ማለት እና «ወላዲ» ማለት «ወልድ» ማለት እና «ተወላዲ» ማለት «መንፈስ ቅዱስ» ማለትና «ሠራጺ» ማለት ልዩ ልዩ እንደሆነ ይናገራል:: ወልድ ከሦስቱ አካላት አንዱ ሲሆን በተለየ አካሉ ሰው የሆነበትን ምሥጢር ያሳያል:: መለኮት የሚለውን ቃል በልዩ ልዩ ሥልት ተርጉሞ ያሳያል:: «ኃይል» «ክሂል» «ሥልጣንም" በአካል ከሦስት የማይከፈሉ መሆናቸውን ያስተምራል:: በአጠቃላይ ይህ መጽሐፍ ለትምህርተ መለኮት ደቀ መዛሙርት እና በሃይማኖት ለማደግ በትምህርተ ሥላሴ ለመራቀቅ በሃይማኖት ትምህርት ለመላቅ ለሚፈልጉ ሁሉ ግሩምና ድንቅ መልዕክት የያዘ መጽሐፍ ነው:: እኔም ይህን ጽሑፍ ለማንበብ ባገኘሁት ጊዜ ለንባብ በሚያዳግት ታይፕ ተጽፎ አንድ መቶ ገጽ ያለው ሆኖ አገኘሁት:: በአነበብኩት ጊዜ በጣም የበሰለ «ትምህርተ መለኮት» የተገለጠበት ትምህርተ ሊቃውንት ሆኖ አገኘሁት:: በመሆኑም የቀደሙት ሊቃውንት አስተምህሮ ለትውልድ እንዲተላለፍ በማድረግ የበኩሌን አስተዋጽኦ ለማድረግ እንደገና አቅንቼ ጽፌ ለአንባቢ በሚመች መንገድ አቅርቤዋለሁ» በማለት መምህር ልዑለቃል አካሉ ይናገራሉ።

በአባ ማትያስ የተዘጋጀው «ፍኖተ ሕይወት» የተሰኘው መጽሐፍም ከገጽ ፩ እስከ ገጽ ፹፭ ድረስ ይህንን ደገኛ «ፍኖተ እግዚአብሔር» የተሰኘ መጽሐፍ ሙሉውን በቀጥታ ገልብጦታል። ምናልባት ሲገለብጡ የሐሳብ ማቀዳደም ሊኖር ይችላል እንጅ ሙሉው ተገልብጧል። ገጽ ፭ ላይ ግን ሲገለብጡ የጽሕፈት ስህተት ተሠርቷል። ይኸውም «አንድ መለኮት በሦስት መለኮትና በሦስት አካላት ህልው ኾኖ» የሚል ነው። ፍኖተ እግዚአብሔር ላይ ግን «አንድ መለኮት በሦስት አካላት ህልው ኾኖ» ሲል ይገኛል። «ፍኖተ ሕይወት» ላይ የተሠራው መለኮትን ሦስት የማድረጉ ስህተት ሆን ተብሎ የተሠራ እንዳልኾነ ግን አስባለሁ።

«ፍኖተ እግዚአብሔር»ን ገልብጠው ሲጨርሱ ትንሽ የምስጋና መደምደሚያ አክለዋል። ፍኖተ እግዚአብሔር ሲጨርስ ከተጠቀመበት መደምደሚያ ፍኖተ ሕይወት ላይ በትርፍነት የተጨመረው «ሦስተኛም ከልጇ ከወዳጇ አማልዳ በነፍስ በሥጋ የምታድነን እግዝእትነ ማርያምን በማኅፀነ ሐና ፈጥሮና ከአንስተ ዓለም መርጦ የሰጠን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን አሜን» የምትለዋ ብቻ ናት። ስለዚህ «ፍኖተ ሕይወት» የተሰኘው መጽሐፍ እስከ ገጽ ፹፭ ድረስ «ፍኖተ እግዚአብሔር» የተሰኘውን የአለቃ ኅሩይን መጽሐፍ የያዘ ነው።

ከዚህ በመቀጠል እዚሁ ገጽ ፹፭ ላይ የሚጀምረው አዲስ ርእስ «የሥላሴ ዘላለማዊ ህልውና» የሚለው ሀሳብ ደግሞ «ወልደ አብ» ገጽ ፭፭ ላይ የሚጀምረው ሀሳብ ነው። «ወልደ አብ» የተባለው መጽሐፍ በቅብዐቶች የታተመ እና በ፲፱፻፲ ዓ.ም የጥቅምቱ ቅዱስ ሲኖዶስ የተወገዘ መጽሐፍ ነው። «ፍኖተ ሕይወት» ላይ አባ ማትያስ የገለበጡት ከ«ወልደ አብ» ይኹን ወይም «ወልደ አብ» ከአባ ማትያስ «ፍኖተ ሕይወት» የተገለበጠ ይኹን ግን የሚታወቅ ነገር የለውም። ምክንያቱም ኹለቱም መጻሕፍት የታተሙበት ዘመን የተገለጠ ስላልኾነ ይህ ነው ማለት ሊከብድ ይችላል። ነገር ግን ኹለቱ መጻሕፍት የሚያመሳስላቸው ባሕርይ እስካለ ድረስ ከየትም ይገልበጥ ከየት ችግሩን መዘርዘር ግድ ይላል። «ፍኖተ ሕይወት» ከ«ወልደ አብ» መጽሐፍ ላይ ሲገለብጥ አንዳንዶችን ከ«ወልደ አብ» ውጭም አስፍቶ ጽፏል አንዳንዶችን ደግሞ ከ«ወልደ አብ» አጥብቦ ጽፏል።

ገጽ ፹፰ ላይ «ቅጥነተ ሕሊናሆሙ ለመንፈሳውያን በጎበ ቅጥነቶሙ ለሥላሴ ከመ ሥጋ ገዚፍ እንዳለ አረጋዊ መንፈሳዊ» እስከሚለው ድረስ ከ«ወልደ አብ» ከወሰዱ በኋላ «ሥላሴ ቅድመ ዘመን ይመስገኑ ነበር ካሉ» ብለው ከ«ወልደ አብ» ተለይተው አዲስ ሃሳብ ጀምረዋል። የሀሳብ መቀዳደም ግን እንዳለ አስተውያለሁ። «ወልደ አብ» ዘግይቶ የጻፈውን «ፍኖተ ሕይወት» አስቀድሞ፣ «ወልደ አብ» አስቀድሞ የጻፈውን «ፍኖተ ሕይወት» አዘግይቶ ሲጽፍ ብዙ ቦታዎች ላይ ተመልክቻለሁ። ሥነ ፍጥረትን የተመለከተው የ«ፍኖተ ሕይወት» ማብራሪያ ከ«መጽሐፈ አክሲማሮስ» የተወሰደ ስለኾነ ደስ ይላል። «ወልደ አብ» የተባለው የቅብዐቶች መጽሐፍ ሥነ ፍጥረትን ርእሱን ጽፎ አንድ ገጽ ማብራሪያ ከሰጠ በኋላ ወደ ሌላ ርእስ ይገባል። «ፍኖተ ሕይወት» ግን እዚህ ላይ በየዕለቱ የተፈጠሩ ፍጥረታትን ከሰፊ ማብራሪያ ጋር ይዟል።

ከዚህ በኋላ ገጽ ፪፯፯ ላይ የሚጀምረው «አምስቱ አእማደ ምስጢር» የሚለው ርእስ «ወልደ አብ» ገጽ ፭ ላይ የሚጀምረው ሀሳብ ነው። ከዚያ በኋላ «እንናገራለን» ብለው ከጨረሱ በኋላ ወደ «ወልደ አብ» መቅድም ገጽ ተመልሰው መቅድም ገጹን ሙሉውን ወስደውታል። በነገራችን ላይ «ወልደ አብ» የቅብዐቶች ስለኾነ ከቅብዐቶች መጽሐፍ ለምን ይገለብጣሉ? ማለት አይቻልም። ምክንያቱም እውነት የኾነውን የእኛ ትምህርት ይዘው ቅብዐቶች የጨመሩት ሥርዋጽ ሊኖርበት ስለሚችል እንጅ «ፍኖተ ሕይወት» ላይ እስከዚህ ገጽ ድረስ የተሳሳተ አነጋገር አላየሁበትም። ከቅብዐቶች ጋራም የምንለያየው ምስጢረ ሥጋዌ ላይ እንጅ ስነ ፍጥረት ላይ ስላልኾነ አምስቱ አእማደ ምስጢር መግቢያ ላይም የከፋ ስህተት አላየሁም።

«ፍኖተ ሕይወት» እና «ወልደ አብ» አንድ ኾነው የሚገናኙት ምስጢረ ሥጋዌን ሲጀምሩ ነው። «ፍኖተ ሕይወት» ገጽ ፪፻፲ ላይ «የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምንድን ነው ቢሉ ማንጻት፣ መክፈል፣ ማዋሐድ፣ መፍጠር፣ ማጽናት ነው» ሲል «ወልደ አብ» ግን ገጽ ፪፻፳፭ ላይ «ማጽናት» የሚለውን «ቅብዕ መኾን» ብሎ መዘግቦታል። በዚህ ሃሳብ ላይ ከ«ወልደ አብ» በተሻለ «ፍኖተ ሕይወት» ጥሩ ጽሑፍ ጽፏል። «መፍጠር» የሚለው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ «ሥግው ቃል ተፈጥሯል» በሚለው ሀሳብ ላይ «ወልደ አብ»ም «ፍኖተ ሕይወት»ም አንድ ኾነው ይገኛሉ። «ፍኖተ ሕይወት» ገጽ ፪፻፲፰ ላይ «ሥግው ቃል እንደተፈጠረ» አብራርቷል። ይህ ደግሞ አርዮሳዊነት ነውና ይህንን በተመለከተ ወደፊት በሰፊው የምናብራራ ስለሚኾን ያን ጊዜ እንመለከተዋለን። የመንፈስ ቅዱስ ሥራ «ቅብዕ መኾን ነው» የሚለውን ሀሳብ በዚህ ገጽ ላይ ባይጽፉትም ወደፊት በሚያብራሩት ጽሑፍ ላይ ግን አልፈው አልፈው ጣል ሲያደርጉ ይታያሉ።

እግዚአብሔር ቢፈቅድ ወደፊት ስለዚህ መጽሐፍ በሰፊው የምንመለከት ይኾናል። ይህን መጽሐፍ የምታከፋፍሉ የምትሸጡ ግን ቆም ብላችሁ ልትመረምሩት ይገባል። መጽሐፉ መገኘት በሌለበት ቦታ እንኳ እየተሸጠ እንደኾነ በውስጥ መስመር ብዙዎች ጠቁመውኛል። ለምሳሌ ደብረ ብርሃን እና ድሬዳዋ ማዕከላት ላይ በማኅበረ ቅዱሳን ሱቅ ዋናውን ማዕከል ጨምሮ እየተሰራጨ እንደኾነ ይታወቃል። መጽሐፉ ችግር የለበትም የምትሉ ካላችሁ ግን እኔ ተሳስቼ ከኾነ ልታርሙኝ ሙሉ መብት አላችሁ። በዚሁ አጋጣሚ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንም ይህን መጽሐፍ እንድትመረምሩት በትሕትና እጠይቃለሁ። ማኅበረ ቅዱሳን እንዲህ ያለ ስህተት ሲሠራ አይቸ አላውቅም። ኢዲቶርያል ቦርዱ አይቶ ተመልክቶ ገምግሞ የሚያስቀር እና የሚያሳልፍ ስለኾነ ከዚያ እውቅና ውጭ በተወሰኑ ግለሰቦች የገባ ሊኾን እንደሚችል አስባለሁ።

«ወልደ አብ» ገጽ ፪፸፯ እና «ፍኖተ ሕይወት» ገጽ ፪፻፲፭ ያላቸው ዝምድና ምንድን ነው? ፍኖተ ሕይወት ገጽ ፪፻፲፭ ላይ «መፍጠርስ እንዴት ነው? ቢሉ ነፍስ የሚኾነውን ባሕርየ ሥጋ ማድረግ ነው። ፈጣሪ ማለት ዓይን ጆሮ አፍንጫ ከንፈር እጅና እግር የቀረጸ ማለት ነው። ከአባት ዘር ከእናት ደም ተከፍሎ ተዋሕዶ እንዲፈጠር ወልድም ከእመቤታችን ደመ ድንግልናዋን ከፍሎ ተዋሕዶ ተወልዷልና እንደ ዘርዐ ብእሲ የኾነ ወልድ ነው፤ ሳይዋሐድ አልፈጠረም ተዋሕዶም ሳይፈጠር አልቆየም ሲዋሐድ ሲፈጠር ፭ ጊዜ ነው። የዘርዐ ብእሲስ ደምነቱን ለቆ አንድ አካልና አንድ ባሕርይ ይኾናል። የወልድና የደመ ድንግልና ተዋሕዶ ግን አካሉ ሳይጠፋ ነው» ይላሉ። የፊደል ግድፈቶች ራሱ አለመስተካከላቸው የወልደ አብን ሶፍት ኮፒ ተረክበው አሳጥረው የወሰዱት ይመስለኛል።

ከላይ «ፍኖተ ሕይወት» ላይ ተጽፎ የምናገኘው ምንፍቅና ወልደ አብ ገጽ ፪፸፯ እና ፪፸፯ ላይ በተከታታይ የተጻፈ ነው። «እንደ ዘርአ ብእሲ የሆነው ወልድ ነው ማለት እንዴት ነው ቢሉ። ከአባት ዘር ከእናት ደም ተከፍሎ ተዋሕዶ እንዲፈጠር ወልድም ከእግዝእትነ ማርያም በኅብረ መንፈስ ቅዱስ ከተከፈለ ደመ ድንግልና ጋራ ተዋሕዶ ተፈጥሯልና። እንደ ዘርአ ብእሲ የሆነ ወልድ ነው ማለት ስለዚህ ነው» ወልደ አብ ገጽ ፪፸፯። ወልደ አብ ገጽ ፪፸፯ ላይ ደግሞ ሲፈጠር እና ሲዋሐድ አንድ ጊዜ እንደሆነ ይናገራሉ “... ተዋሕዶ ተፈጠረ ሳይዋሐድ አልተፈጠረም። ተዋሕዶ ሳይፈጠር አልቆየም። ሲዋሐድ ሲፈጠር አንድ ጊዜ ነው። ከተፈጥሮ ተዋሕዶ ቀደመ ባሉ ጊዜ ከቅብዓትም ተዋሕዶ ቀደመ ማለት ይሆናል” ወዘተ በማለት ይጽፋሉ።

ሙሉውን ከኹለቱም መጻሕፍት እያነጻጸራችሁ እንድትመለከቱ እጠቁማችኋለሁ። «ተዋሕዶ ተፈጠረ» በሚለው የመጀመሪያው ስህተት ላይ «ፍኖተ ሕይወት» «ደመ ድንግልናዋን ከፍሎ ተዋሕዶ ተወልዷልና» በማለት ሲጽፍ ወልደ አብ ላይ «ወልድም ከእግዝእትነ ማርያም በግብረ መንፈስ ቅዱስ ከተከፈለ ደመ ድንግልና ጋራ ተዋሕዶ ተፈጥሯልና» በማለት ጽፈዋል። በዚህ በመጀመሪያው የክህደቱ መግቢያ ላይ «ፍኖተ ሕይወት» የተሻለ ነገር ይዟል። «ተዋሕዶ ተፈጠረ» በማለት ፈንታ «ተዋሕዶ ተወልዷልና» ስላለ ይሻላል። ነገር ግን ቀጣይ በሚመጡ ጽሑፎች ላይ «ተዋሕዶ ተፈጠረ» ማለቱ ስላልቀረ ችግሩን ሙሉ በሙሉ አልቀረፈም ክህደቱንም ሙሉ በሙሉ አላስወገደም። ምክንያቱም በሚቀጥለው ጽሑፉ ላይ «ሳይዋሐድ አልፈጠረም ተዋሕዶም ሳይፈጠር አልቆየም ሲዋሐድ ሲፈጠር ፮ ጊዜ ነው» ብሏልና። አካላዊ ቃል ሥጋን ሲዋሐደው ሥጋ ክቡር አምላክ ኾኗል እንላለን እንጅ በተዋሐደ ጊዜ ተፈጠረ አንልም። ቃል ሲዋሐደው ፍጡሩ ሥጋ ከብሮ አምላክ ኾነ ይባላል እንጅ ቃል ስለተዋሐደው የሥጋ ፍጡርነት ቃልን ፍጡር ያደርገዋል ሊባል እንዴት ይቻላል?

በነገራችን ላይ ተዋሕዶ ማለት ግን አንድ መኾን ማለት አይደለም እንዴ? ታዲያ አንድ ነው ካልን ማን ነው ተፈጠረ የሚባለው? ሥጋ ነው እንዳትሉን ሥጋማ መጀመሪያውንም ፍጡር ነው፤ ቃል ነው እንዳትሉን አካላዊ ቃል ሥጋን ሲዋሐድ ሥጋ አምላክ ይኾናል እንጅ ፈጣሪ ወደ ፍጡርነት ሊቀየር እንዴት ይችላል? ሥግው ቃል ነው የተፈጠረ ካላችሁ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን ፍጡር ነው ማለታችሁ ነውና ከአርዮስ በምን ተለያችሁ? አርዮስ በመለኮቱ ፍጡር ስላለው እንጅ በሥጋው ፍጡር ቢለው ባልተሳሳተም ነበር የምትሉትም ሸውራራ ትምህርታችሁ ተዋሕዶን እንደማታውቁት ማሳያ ነው። ከተዋሕዶ በኋላ ይህ ሥጋ ነው ይህ ደግሞ መለኮት ነው ሊባል እንዴት ይቻላል? አንዱ ለስንት ይከፈላል? ለስንትስ ይሰነጠቃል?

ሌላው ወልደ አብ ላይም ፍኖተ ሕይወት ላይም የምናገነው «እመንፈስ ቅዱስ» የሚለውን ግብረ መንፈስ ቅዱስ መተርጎም ላይ ያለ ጠማማ ትምህርት ነው። ፍኖተ ሕይወት ገጽ ፪፻፲፭ ላይ «መናፍቃን ግን ተሰብአ እመንፈስ ቅዱስ ያለውን ይዘው ከመንፈስ ቅዱስ ዘርእ ከማርያም ደም ተከፍሎ ወልደ ተፈጠረ ብለዋል» ይላል። መናፍቃን ሊሉቸው የቻለ መንፈስ ቅዱስን እንደ ዘርእ ብእሲ አድርገው የሚቆጥሩትን ሰዎች እንጅ ወልድ ተፈጠረ የሚሉትን አለመኾኑን ግልጽ ነው። ከማርያም ደም ተከፍሎ ወልድ ተፈጠረ ቢሉ ኖሮ ግን መናፍቅ አይባሉም ነበር በዚህ መጽሐፍ ትምህርት መሠረት።

ገጽ ፪፻፲፯ ላይም «ከመንፈስ ቅዱስ ዘር ተከፍሎ ወልድ ተፈጠረ ሲል አይደለም ብሏል» በማለት «እመንፈስ ቅዱስ» ያለውን ሲተረጉሙ ይታያሉ። «ከመንፈስ ቅዱስ ዘር ተከፍሎ» የሚለው ቢወጣ ግን እውነት ይኾን ነበር ማለታቸው ነው። በእውነት «እመንፈስ ቅዱስ» ሲሉ ሊቃውንት ምን ማለታቸው ነው። ጸሎተ ሃይማኖት ላይ ያለውን ብቻ ትርጓሜ በአጭሩ ላቅርብላችሁ። «ተሰብአ ወተሰገወ እመንፈስ ቅዱስ። ወተሰብአ እመንፈስ ቅዱስ ይላል አብነት እም፣ በ፣ ነው በግብረ መንፈስ ቅዱስ። ሐተታ የከፈለ ያነሳ ያዋሐደ መንፈስ ቅዱስ ነውና ወእማርያም እምቅድስት ድንግል። እም እና እም አንድ ወገን ነው እመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ሰው የሆነ። አንድም መንፈስ ቅዱስ ከመከፈሉ የተነሣ እመቤታችን ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ ከማለቷ የተነሣ ሰው የሆነ» በማለት ሊቃውንቱ ይተረጉማሉ።

ፍኖተ ሕይወት ገጽ ፪፻፲፰ ላይ «ይከፈል ብለው ቢያዙ ከእመቤታችን ደመ ድንግልና ተከፈለ። ይፈጠር ብለው ቢያዙ ወልድ ከደመ ድንግልና ተዋህዶ ተፈጠረ። ወልድንም በሰውነቱ አርእስት ፍጡር ማለት ይገባል? እንደ አርዮስ ክህደት አይኾንም? ቢሉ አርዮስስ በመለኮቱ ፍጡር ቢለው ክህደት ኾነበት እንጅ በሰውነቱ ፍጡር ቢለውስ ክህደት ባልኾነበትም በመለኮቱ ግን ፍጡር ቢለው ክህደት ኾኖበታል» ይላሉ። ይኸው አገላለጽ ወልደ አብ ገጽ ገጽ ፪፴፰-፪፴፭ «ወልድ በሰውነቱ ፍጡር ይባላል። ወልድንማ ፍጡር ብንለው እንደ አርዮስ ክህደት አይሆንብንም ቢሉ አርዮስ በመለኮቱ ፍጡር ቢለው ክህደት ሆነበት እንጅ በሰውነቱ ፍጡር ቢለው ክህደት ባልሆነበትም ነበር። ነገር ግን በመለኮቱ ፍጡር ቢለው ክህደት ሆነበት» ይላል። እዚህ ላይ የምጠቁማችሁ የኹለቱን መጻሕፍት ተመሳሳይነት እንጅ ወልደ አብን ስንመለከት መልስ የሰጠንባቸው ክህደቶች ናቸው ድጋሜ እያየናቸው ያሉትና ዳግም መልስ መስጠት አልፈልግም።

የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ «ፍኖተ ሕይወት» የተባለውን መጽሐፍ ሊቃውንቱ እንዲመረምሩት መነሻ ሃሳብ ማቅረብ እና ይህ መጽሐፍ ትክክል ነው ብለው ባለማወቅ የሚያከፋፍሉ ሰዎች ራሳቸውን ቆም ብለው እንዲፈትሹት ማስደረግ ነው።

አባ ማትያስ የጻፉት #ፍኖተ_ሕይወት መጽሐፍ ገጽ ፪፻፲፱ ላይ «ሥጋን በቃልነቱ ፈጣሪ እንዳሉ ቃልን በሥጋነቱ ፍጡር ማለት ይገባል? ንብሎ ፈጣሬ በእንተ ከመ እግዚአብሔር ወአምላከ ወዓዲመ ንብሎ ፍጡረ በሥጋ በእንተ ዘተወልደ እምብእሲት እንዳለ #ቂርሎስ፤ ቃልንስ በሰውነቱ ፍጡር ካላሉ ሥጋን በቃልነቱ ፈጣረ ማለት አይገባም» ይላሉ።

ገብረ መድኅን እንዳለው የጻፉት #ወልደ_አብ ገጽ ፪፴፭ «ወልድንም በሰውነቱ #ፍጡር ብሎ ማመን ይገባል። ለሊሁ ፈጣሪ በእንተ ከመ ውእቱ አምላከ ወእግዚአብሔር ውእቱ ወዓዲመ ንብሎ ፍጡረ እስመ ውእቱ ተወልደ እምብእሲት እን ቅዱስ #ቂርሎስ ሃ አ ስምዓት ክ ፪ ቁ ፲፱ ሥጋ በመለኮት ርስት ፈጣሪ ነው። መለኮት በሥጋ ርስት ፍጡር ነው። ሥጋ ሲፈጠር መለኮት ከሥጋ ጋራ ተዋሕዶ አብሮ ተፈጠረ ካላሉ እንደ ንስጥሮስ ፪ አካል ማድረግ ኃደረ በብእሲ ማለት ነውና ክህደት ነው» ይላሉ።

እዚህ ላይ እንዲያውም ወልድን #ፍጡር ነው ብሎ የማያምን ሰው እንደ ንስጥሮስ ኹለት አካል ኹለት ባሕርይ ወደሚል ክህደት ይገባል ይላሉ። ይህ ስህተት ንስጥሮስ ምን ብሎ እንደካደ ካለማወቅ እና የተዋሕዶን ረቂቅ ምስጢር ካለመረዳት የሚመጣ በሽታ ነው። ሥጋን ፈጣሪ ኾነ ስላልን የግድ አካላዊ ቃልን ፍጡር ማለት አለብንን? አዎ ካሉ እዚህ ላይ ነው ንስጥሮሳዊነት ነው የሚታየው ምክንያቱም አንዱን አካል ለኹለት አንዱንም ባሕርይ ለኹለት ከፍለውታልና ንስጥሮሳዊነት ነው።

በግዕዝ ጽፈው በደረቁ ያለፏትን ነገር ከመጽሐፉ ብንመለከተው መልካም ነው። ሃይማኖተ አበው መጽሐፋችን ላይ ስምዐት ፪፻፲÷፲፱ ላይ «ለሊሁ ፍጡር ወለሊሁ ፈጣሪ ንብሎ ፈጣሪ በእንተ ከመ ውእቱ አምላከ ወእግዚአብሔር ውእቱ ወዓዲመ ንብሎ ፍጡረ እስመ ውእቱ ተወልደ በሥጋ እምብእሲት» የሚል ነው። ወልደ አብ እና ፍኖተ ሕይወት ላይ የተጠቀሰውን ጥቅስ እና ሃይማኖተ አበው ላይ ያለውን የጻፍኹላችሁን ጥቅስ አመሳክሩት ቆርጠው ነው የቀጠሉት።

ወደ አማርኛ ሲመለስም «እርሱ ሰው ነው እርሱም አምላክ ነው። እግዚአብሔር ስለኾነ ፈጣሪ እንለዋለን ወዲህም ከድንግል በሥጋ ስለተወለደ ሰው እንለዋለን» ይላል። «ፍጡረ- ሰው ኾነ» ተብሎ ተተርጉሞ ነው የምንመለከተው። መጻሕፍት «ፍጡረ» የሚለውን ቃል «ፍጡር ሥጋን» በማለትም እያቀኑ ይተረጉማሉ እንጅ በቀጥታው ወልድን ፍጡር ነው ሲሉ አይገኙም። ያማ ቢኾን ኖሮ አርዮስስ ምን ዕዳው ነበራ? ለምን ተወገዛ? አርዮስ ወልድን ፍጡር ያለው በመለኮቱ ነው እኛ ቅብዐቶች ግን ወልድን ፍጡር የምንለው በሰውነቱ ነው ትሉኝ ይኾናል። በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ከኾነ በኋላ ይህ ፍጡር ነው ይህ ደግሞ ፈጣሪ ነው ትለው ዘንድ እንዴት ይቻላል? ፍሕምን ይህ ከሰል ነው ይህ ደግሞ እሳት ነው ብለህ ትከፍለው ዘንድ እንዴት ትችላለህ?

እነርሱ የሚሉት ሥጋን በመለኮት ርስት ፈጣሪ ነው ካልነው መለኮትንም በሥጋ ርስት ፍጡር እንለዋለን ነው። እኛ ግን በተዋሕዶ አንድ ኾኗልና ከተዋሕዶ በኋላ ይህ ሥጋ ይህ መለኮት ብለን አንከፋፍለውም። አምላክ ሲኾን ሰው ሰው ሲኾን አምላክ ኾኗል እንላለን እንጅ። ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው እንለዋለን። መለኮትን በሥጋ ርስት ሰው ኾነ እንለዋለን ሰውም ስለኾነ የማይዳሰሰውን መለኮት ዳሰሰነው፣ ዘመን የማይቆጠርለትንም መለኮት ዘመን ቆጠርንለት፣ ምሉዕ የኾነውንም መለኮት በጠባብ ደረት በአጭር ቁመት ተወሰኖ አየነው። ሥጋንም በመለኮት ርስት አምላክ ኾነ እንለዋለን። አምላክ በመኾኑም ሥጋ የሚዳሰሰው የማይዳሰስ የሚጨበጠው የማይጨበጥ መለኮት ኾኗል ዘመን የሚቆጠርለት ዘመን የማይቆጠርለት ዘለዓለማዊ ኾኗል እንላለን።

ሥጋን በመለኮት ርስት በጠራንበት መለኮትንም በሥጋ ርስት የግድ መጥራት አለብን ብሎ እንደ ቅብዐቶች እና እንደ አባ ማትያስ ያለ ስህተት ላይ መውደቅ አይገባም። ሥጋን በመለኮት ርስት ፈጣሪ ነው ካልን የግድ መለኮትንም በሥጋ ርስት ፍጡር ነው ማለት አለብን ብለው የማያባራ ክህደታቸውን ካዘነቡብን እስኪ ይህንን ይመልሱልን እንጠይቃቸው።

ሥጋን በመለኮት ርስት ጻድቅ ነው ስላልን መለኮትን በሥጋ ርስት ሐሳዊ ነው ልትሉት ነውን?

ሥጋን በመለኮት ርስት ቅዱስ ነው ስላልን መለኮትን በሥጋ ርስት ጎጥእ ነው ልትሉት ነውን?

ይህ በአባ ማትያስ የተጻፈው ፍኖተ ሕይወት ከወልደ አብ ጋር ያለውን ልዩነት እስኪ ተመልከቱት ምንድን ነው ልዩነቱ? ታዲያ ወልደ አብ ይወገዝልን ብለን ፊርማ ስንሰበስብ ኖረን ዛሬ በራሳችን ሱቅ እንዴት ሊከፋፈል ይችላል? ይህ የዘወትር ጥያቄዬ ነው። ወልደ አብን አሳጥረው የገለበጡት አባ ማትያስ ማን እንደኾኑ ግን የምታውቁ ሰዎች ብታሳውቁን መልካም ነው። ሊቃውንቱ መነሻ ሃሳብ እንዲኖራቸው የተጻፈ ነው። መጽሐፉን የሚያከፋፍሉ የማኅበረ ቅዱሳን ሱቆችም ራሳቸውን እንዲያስተካክሉ የተጻፈ ነው።

ማመሳከር እንድትችሉ ፍኖተ ሕይወት ላይ ያለውን እና ወልደ አብ ላይ ያለውን ጽሑፍ ከዚህ ጋር አብሬ አያይዠላችኋለሁና አንብቡት።

ከዚህ በፊት «ወልድ ፍጡር» በሚለው የፍኖተ ሕይወት እና የወልደ አብ አገላለጥ ላይ አንድ ክፍል ጽፌያለሁ። አሁንም ቢኾን «ወልድ ፍጡር» አልልም ምንም ማስረጃ ብታቀርቡልኝ በዚህ መቼም ቢኾን የምስማማ አይደለሁም። «መጻሕፍት እንዲህ ሲሉ ነው» እያልን እያቀናን ልንተረጉመው እንችል ይኾናል እንጅ በቁሙ «ወልድ ፍጡር» የሚል አስተምህሮ አላውቅም።

«ፍጹም አካሉን ፈጠረ»፣ «ሥጋን ፈጥሮ ተዋሐደ»፣ ሥጋን ፍጥሮ ሲዋሐድ ማንም አላገዘውም ራሱ ፈጠረው እንጅ» ወዘተ እያሉ በሃይማኖተ አበው ውስጥ የተገለጡ ጥሬ ቃላት አሉ። እነዚህ ጥሬ ቃላት አካላዊ ቃል ሥጋን ሲዋሐድ፣ የዕለት ጽንስ ሲኾን፣ ደመ ድንግልናዋን ሲከፍል በጊዜ ተዋሕዶ የተደረገውን ሕዋሳት መቅረጽ ያደረገውን ሥራ «ፈጠረ» በሚል መጻሕፍት ጽፈውት እናገኛለን። «ፈጠረ» ሲል አንድም «ፍጡር ሥጋን ተዋሐደ» በማለት ምትሐት አለመኾኑን ሲያስረዳ ነው። አንድም «ሕዋሳትን ቀረጸ ማለትም ዓይን ጆሮ እግር እጅ አፍንጫ ወዘተን ቀረጸ» ሲል ነው እንጅ ዛሬም በየማኅጸኑ አዲስ ፍጥረት ይፈጥራል ሲል አይደለም። «ፈጠረ» ሲል አንድም ሰው ኾነ ሲል ነው።

እስካሁን ያየነው «ፈጠረ» የሚለው ቃል በጊዜ ተዋሕዶ ብቻ የምንናገረው ቃል እንጅ ከተዋሕዶ በኋላም በቃል እና በሥጋ ርስት እያልን አንዱን ኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋው ፍጡር በመለኮቱ ፈጣሪ እያልን የምንናገረው አይደለም። ታዲያ በሥጋው ፍጡር በመለኮቱ ፈጣሪ ካልነው ተዋሕዶው የት አለ? የእኔ ጥያቄም ይኸው ነው። መጻሕፍትን ጠቅሳችሁ ለምትከራከሩኝ ኹሉ «ከተዋሕዶ በኋላ በሥጋው ፍጡር ነው በመለኮቱ ፈጣሪ ነው» ልንለው እንችላለን ወይ? የሚለውን መልሱልን።

በማኅፀን የሠራውን ሥራ ከማኅፀን ውጭም እንዳደረገው አድርገን ተዋሕዶውን ከዘሬጋነው ችግር ነው። ደመ ድንግልናዋን ሲከፍል፣ ቃል ሥጋን ሲዋሐድ፣ ሥጋ አምላክ ሲኾን (ሲከብር)፣ ሲጸነስ፣ ሕዋሳትን ሲቀርጽ (በመጻሕፍት አገላለጥ ሲፈጥር) አንድ ጊዜ ነው መቀዳደም የለም። ከዚህ በኋላ ግን «ፈጠረ» «ተፈጠረ» የሚለውን አገላለጥ ልንጠቀመው አንችልም። ክርስቶስን «ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው» እንለዋለን እንጅ «ፍጹም ፍጡር» የሚባል አገላለጥ አይቼ ሰምቼ ተምሬ አላውቅም። «ፍጹም ፍጡር» የሚል አገላለጥ አለ ካላችሁ አሳዩኝ። ለምሳሌ በዘመነ ሥጋዌው ማለደ፣ ጸለየ፣ ለመነ ወዘተ እያልን የተጠቀምንባቸውን ቃላት በመስቀል ላይ ቤዛ ኾኖ ደሙን አፍስሶ ነጻነትን ከሰጠን በኋላ ልንጠቀምባቸው አንችልም። ዛሬ ድረስ «ይማልዳል» «ይለምናል» «ገንበስ ቀና እያለ ይሰግዳል» ወዘተ እያሉ የተሳሳቱት እኮ ይህን ከመስቀል በፊት የተገለጠውን አነጋገር ዛሬ ድረስ እየተጠቀሙበት ስለኾነ ነው። ታዲያ «ፈጠረ» ላይ ያለውንስ እንደዚህ ያያችሁት አይመስላችሁምን?

ወደ ዛሬው ጉዳይ እንግባና ጥቂት እንበል። «ፍኖተ ሕይወት» ላይ የጌታ ጽንሰት የሚለው ርእስ እና «ወልደ አብ» ላይ ነገረ ማርያም የሚለው ርእስ በብዙ ነገራቸው ይመሳሰላሉ። ነገር ግን «ወልደ አብ» በቅብዐተ መንፈስ ቅዱስ ከበረ ብሎ ይደመድማል «ፍኖተ ሕይወት» ግን በተዋሕዶ ከበረ ብሎ ያስራል። በዚህ ርእስ ላይ ከወልደ አብ ይልቅ «ፍኖተ ሕይወት» በጥሩ መልኩ በተዋሕዶ ከበረ ማለትን አስረድተዋል።

«ፍኖተ ሕይወት» ገጽ ፪፻፴፭ መጨረሻ አካባቢ «ጌታም ለአብሥሮተ ድንግል ገብርኤልን መስሎ ሲወጣ ሲወርድ ስለታየ «ወረደ እምሰማያት» አለ እንጅ ሰማይን ለቆ ወረደ ሲል አይደለም። ያበሠራት ጌታ ነውን? ቅዱስ ገብርኤል አይደለምን? ቢሉ ገብርኤልን መስሎ ሲወጣ ሲወርድ ስለታየ ገብርኤል ነው እንላለን እንጅ እርሱ ቃለ እግዚአብሔር አብሥሮ አደረባት» ይላል። ይኸው አገላለጥ «ወልደ አብ» ገጽ ፪፻፯ ላይ ተጽፎ ይገኛል። ከታች ኹለቱንም በፎቶ ስላያያዝኩላችሁ ተመልከቱት።

የእኔ ጥያቄ ያበሠራት ገብርኤል ነው ወይስ አካላዊ ቃል ነው? የሚለው ነው። «ይኩነኒ» ስትለው ወዲያኑ አካላዊ ቃል ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ወዲያውኑ ተጸነሰ እንላለን። ይህ ወዲያኑ መደረጉ የፍጡር ብሥራት ቢኾን ኖሮ በዘገየ ነበር የሚሉ ስላሉ ያበሠራት አካላዊ ቃል ራሱ ነው ሊባል የሚችልበት ነገር ያለ አይመስለኝም። ምናልባት መጽሐፍ ላይ ያገኛችሁት ነገር ካለ አሁንም ልታስረዱኝ ትችላላችሁ። እኔ የማውቀው ያበሠራት ቅዱስ ገብርኤል እንደኾነ እንጅ አካላዊ ቃል ገብርኤልን መስሎ ራሱ አብሥሮ አደረባት የሚል ትምህርት አላውቅም። የምታውቁ ካላችሁ ደግሞ መጽሐፍ ጠቅሳችሁ አስረዱኝ። ይኩነኒ ስትለው ወዲያውኑ ማደሩን ሲገልጡ ፍጥነቱን ሲገልጡ እንዲህ ይሉ እንደኾነ እንጅ ያበሠራት ራሱ አካላዊ ቃል ነው የሚለውን ግን አላውቅም።

አባ ማትያስ በተዋሕዶ ከበረ ማለት እና በተዋሕዶ ተቀባ ማለት አንድ ናቸው በማለት ገጽ ፪፻፵-፪፻፵፭ ላይ የገለጡት እና ያብራሩት ነገር በጣም ጥሩ አገላለጥ ነው። «ቀብዐ» ማለት «አከበረ» ማለት ስለኾነ ትርጉሙም ይስማማል። ወልድ ራሱ ቀባዒ ራሱ ተቀባዒ ራሱ ቅብዕ ለመኾኑም የገለጡበት አገላለጥ የሰጡት ማስረጃ በጣም ደስ የሚል ነው። መጽሐፉ በዚህ የጌታ ጽንሰት በሚለው ጽሑፉ ላይ በእኔ አመለካከት እና አረዳድ በውስጡ እውቴ በጥቂት ትምህርቴ ከብሥራተ ገብርኤል ውጭ ይህ ነው የሚባል ስህተት አላየሁበትም። እንዲያም የሚያምር እና ጥሩ የኾነ አገላለጥን የያዘ ነው። ወልደ አብ ላይ አብ ቀባዒ ወልድ ተቀባዒ መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ እያለ ሲያላዝን ፍኖተ ሕይወት ግን አብ ቀባዒ መንፈስ ቅዱስ ቀባዒ ወልድ ቀባዒ ቢልም አንድ ነው ይላል። ወልድን ቀባዒ ተቀባዒ እና ቅብዕ ነው ብሎም ወልደ አብ ላይ ያለውን ወልድ ቅብዕ በተዋሕዶ ከበረ ማለት ኑፋቄ ነው የሚለውን ይሞግታል። የተጠቀሱት ማስረጃዎች የቀረቡት ትንታኔዎችም በጣም ደስ የሚል ነው። በመንፈስ ቅዱስ ከበረ ማለት ኑፋቄ እንደኾነ እና የተወገዘ ትምህርት መኾኑንም የያዘ መጽሐፍ ነው። ከዚህ ቀጥሎ የምናገኘው ተዋህዶ የሚል ርእስ ነው እርሱንም እንዲሁ ወደ ፊት እንመለከተዋለን።